# በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት የትምህርት ቢሮ

**Central Ethiopia Region Government**

**Bureau Of Education**


ቀን/Date: የካቲት 12/2017

ቁጥር/Ref.No: 109/ለ30-1619/ለ7/35

ለ____________________ዞን ትምህርት መምሪያ

ለ________________ልዩ ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት

ባሉበት

**ጉዳዩ፡- ከትምህርት ቤት አመራር ደመወዝ ክፍያ ጋር ተያይዞ ተጨማሪ ሠርኩላር ስለማስተላለፍ፤**

በክልሉ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች በሠለጠኑና የተሻለ የሙያ ብቃት ባላቸው የሰው ሀይል እንዲመሩና የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሰፍን የትምህርት ቤት አመራር ምልመላ፣ መረጣና ምደባ አፈፃጸም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉ ይታወቃል፡፡

በዚሁ መሰረት በውድድሩ ተመርጠው በቋሚነት ለተመደቡ የትምህርት ቤት አመራሮች ለተመደቡበት የስራ መደብ የተፈቀደውን መነሻ ደመወዝ እንዲያገኙ መደረጉን ተከትሎ ነባር የትምህርት ቤት አመራሮች የተሰጣቸው ደመወዝ አቻ መምህራን ከሚያገኙት ደመወዝ ጋር በማነፃጸር ዝቅ ያለ መሆኑን ጠቅሰው በተደጋጋሚ ቅሬታቸውን እያቀረቡ የሚገኙ ከመሆናቸውም በላይ ከዞንና ከልዩ ወረዳ የትምህርት ኃላፊዎች ጋር በተደረጉ ውይይቶችም ጭምር ቅሬታዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ስለሆነም ሙያው የበለጠ ሳቢና ተመራጭ በማድረግ ነባር የትምህርት ቤት አመራሮች ተነሳሽነትና እርካታ ኖሮአቸው የተሰጣቸውን ተልዕኮ በበለጠ ውጤታማነት እንዲያከናውኑ ለማበረታታት ይረዳ ዘንድ ለቅሬታዎቹ ተገቢ ምላሽ መስጠት በማስፈለጉ የተዘጋጀውን ሰርኩላር ከዚህ ደብዳቤ ጋር 1 ገጽ አባሪ በማድረግ የተላከ ሲሆን ከጥር 1 ቀን 2017 ዓ/ም ጀምሮ ለአንድ ጊዜ ብቻ ታሳቢ በማድረግ በጥንቃቄ ተግባራዊ እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

//ከበጎ ምኞት ጋር//

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ትምህርት ቢሮ
Central Ethiopia Regional State Education Bureau

ተሾመ ለምጃቦ ሞሎሮ
Teshome Lemjabo Molloro
ምክትል ር/መስተዳድሩ ጽ/ቤት ኃላፊ
Vice President Office Head

እንዲያውቁት
- ለክቡር ምክትል ርዕሰ መስተዳድር

ግልባጭ
- ለክልሉ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ
- ለክልሉ መምህራን ማህበር ጽ/ቤት
- በመስሪያ ቤታችን
  - ለቢሮ ኃላፊ ጽ/ቤት
  - ለመምህራንና ሠራተኞች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

በያሉበት

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት የትምህርት ቢሮ

Central Ethiopia Region Government

Bureau Of Education

## የሰርኩላሩ አተገባበር፡-

በመምህርነት፣ በርዕሰ መምህርነት፣ በምክትል ርዕሰ መምህርነት እና በሱፐርቫይዘርነት በእያንዳንዱ የተገኙ ልምዶች ተደምረው ከሐምሌ 1/2011 ዓ/ም በፊት ከ18 ዓመት በላይ የስራ ልምድ የነበራቸው ነባር የትምህርት ቤት አመራሮች በትምህርት ቤት አመራር ሪፎርም ተወዳድረው በትምህርት ቤት አመራርነት በሚመደቡበት ጊዜ ለመደቡ የተፈቀደው መነሻ ደመወዝ ሲሰጣቸው፣ የተሰጣቸው ደመወዝ ከአቻ መምህራን አንፃር ሲታይ ዝቅ ሊል እንደሚችል ይገመታል፡፡

በዚሁ ሁኔታ ከነባር የትምህርት ቤት አመራሮች መካከል በሪፎርሙ ተወዳድረው በምክትል ርዕሰ መምህር ወይም በርዕሰ መምህር ወይም በሱፐርቫይዘር ወይም በከፍተኛ ሱፐርቫይዘር የስራ መደብ ላይ በቋሚነት ሲመደቡ ለመደቡ የተሰጣቸው መነሻ ደመወዝ ከአቻ መምህራን አንፃር ሲታይ ዝቅ ያለ ከሆነ ለአቻ መምህራኖቹ የሚከፈለውን መነሻ ደመወዝ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ
Central Ethiopia Regional State Education Bureau



☎ 046-7710712

እባክዎን ምላሽ ሲጽፉ የደብዳቤውን ቁጥር መጥቀስ አይርሱ
In replying, please quote our Ref. No

✉ P.o.Box Worabe